በሙሐመድ ሚስቶች ዙሪያ በርካታ ሴቶች ስለባሎቻቸው ቅሬታ አሰምተዋል። እነዚህ ሚስቶቻቸውን የሚመቱ ባሎች ምርጦች አይደሉም።

ከኢያስ ቢን ዐብደላህ ቢን አቢ ዙባብ -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንደተላለፈው እንዲህ አለ: «የአላህ መልክተኛ - የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - እንዲህ አሉ: "የአላህን ሴት ባሮች አትምቱ!" ዑመርም ወደ አላህ መልክተኛ -
የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - በመምጣት እንዲህ አሏቸው: "ሴቶች በባሎቻቸው ላይ እያመፁ ነው።" የዛኔም
እንዲመቷቸው ፈቀዱ። የነቢዩ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - ሚስቶች ዘንድ በርካታ ሴቶች ስለባሎቻቸው
ቅሬታቸውን አሰሙ። ነቢዩም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - እንዲህ አሉ: "በሙሐመድ ሚስቶች ዙሪያ በርካታ ሴቶች ስለባሎቻቸው ቅሬታ አሰምተዋል። እነዚህ ሚስቶቻቸውን የሚመቱ ባሎች ምርጦች አይደሉም።"» [رواه أبو داود وابن ماجه] [ነው። ሶሒሕ[

ነቢዩ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - ሚስቶችን ከመምታት ከለከሉ። የአማኞች አዛዥ ዑመር ቢን አልኸጧብም -አላህ መልካም ስራቸውን ይውደድላቸውና- እንዲህ አሉ: የአላህ መልክተኛ ሆይ! ሴቶች ባሎቻቸውን ተዳፈሩ። ስነምግባራቸውም ተበላሸ። ነቢዩም - የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - የባልን ሐቅ አለመወጣት እምቢተኝነትን ማሳየት፣ ባልን ማመፅና የመሳሰሉት ምክንያቶች ከተከሰቱ የማያቆስል ምት እንዲመቷቸው ፈቀዱ። ከዛም በኋላ ባሎቻቸው ይህንን ፍቃድ በመጥፎ መንገድ በመጠቀም የሚያቆስል ምት የመቷቸው ሚስቶች የነቢዩ -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - ሚስቶች ዘንድ ቅሬታ ሊያሰሙ መጡ። ነቢዩም -የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - እንዲህ አሉ: ከናንተ ምርጦቹ እነዚያ ሚስቶቻቸውን የሚያቆስል ምት የሚማቱት ወንዶች አይደሉም።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/5821